የሰበር መ/ቁ. 15270

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ሐጎስ ወልዱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የ፤ አለቃ ተሻገር አስታጥቄ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዊስ አው አብዲ

*በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት የሙግት ተካፋይ ስለመሆን - ከሣሽ የመሆን ችሎታ - ፍርድ ቤቱ የክስ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚወስንበት ሁኔታ/በክሱ አቤቱታ ላይ የተገለጸው ነገር የማያስከስስ ሆኖ ሲገኝ/፡- የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33/2/፣ 231/1/ሀ/ - የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67*

በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ የከተማው አስተዳደር በ1982 ለአመልካች የሰጠው በ1945 ዓ.ም. ቦታው ለመ/ሰጭ አባት ተሰጥቶት እያለ በመሆኑ ለመ/ሰጭ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሳይሰረዝ ሌላ ካርታ ለአመልካች መስጠቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የጅጅጋ ዞን ወረዳ ፍ/ቤት በመወሰኑና ውሣኔውም በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡ውሣኔ

የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት፣የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡

1. የከተማ ቦታ በአዋጅ ቁ. 47/67 መሠረት የመንግስት በመሆኑ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡
2. በከተማ ቦታ ላይ ያለን መብት አስመልክቶ ክስ ማቅረብ የሚቻለው ከአዋጅ ቁጥር 47/67 መውጣት በኂላ የመንግስት አካል በሰጠው የይዞታ ወይም የመጠቀም መብት መሠረት ነው፡፡

የሰበር መ/ቁ. 15270

ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- የአስር አለቃ ተሻገር አስታጥቁ

ተጠሪ፡- አቶ አዊል አው አብዲ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘ ነው የተባለን የከተማ ቦታ ለማስመለስ በሚል በሶማሌ ብ/ክ/መ/በጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ የያዘብኝን ቦታ ይልቀቅልኝ በማለት ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የተከሣሽን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የመከላከያ ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ተከሣሽ ክስ የቀረበበትን ቦታ ለከሣሽ ይልቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ



ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም እንደዚሁ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎአል፡፡ የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ማለትም የሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.05/1/8/96 በ15/5/96 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አቤቱታው በዚህ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው የስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተገቢውን ሕጋዊ ሥነ-ስርዓት ተከትለው መወሰን አለመወሰናቸውን ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጉዳዩን ከስር መሠረቱ አንስተን መርምረናል፡፡ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ማየት እንደቻልነው ተጠሪ ክስ ሊመሰርት የቻለው አባቱ የተወልኝን የአፈር ቤትና የውሃ ጉድጓድ ያለበትን በጅጅጋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘውን ቦታ ተከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) በጉልበትና በሕገወጥ መንገድ ይዞብኛል በማለት ነው፡፡ መብቱን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረበው ማስረጃ በ1945 ዓ.ም ለአባቱ ተሰጥቶ ነበር የሚለው የቦታ ይዞታማረጋገጫ ካርታ ብቻ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ቦታው በላዩ ላይ ምንም ዓይነት ቤትም ሆነ ንብረት ያልነበረበትና በማንም ሰው ያልተያዘ መሆኑ ተረጋግጦ በ1982 ዓ.ም በከተማው አስተዳደር የተሰጠው መሆኑን

፣በሰሙ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑን እና በላዩም ላይ ቤት ሰርቶበት ግብርም እየከፈለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ በዚህ ረገድም ማስረጃዎችን አቅርቦአል፡፡ የጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤትም ቦታው ለከሣሽ (ለአሁኑ ተጠሪ) ሊለቀቅ ይገባል በማለት የወሰነው አመልካች (የስር ተከሣሽ) ያቀረባቸው ማስረጃዎች ቦታው በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተሰጠው መሆኑን አያረጋግጡም በሚል ሳይሆን፣ በ1945 ዓ.ም ለከሣሽ አባት የተሰጠው የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሣይሰረዝ ሌላ ካርታ ለተከሣሽ መሰጠቱ ሕገወጥ ነው፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ቦታ በከተማ አስተዳደር ክልል የሚገኝ ማለትም የከተማ ቦታ ነው፡፡ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ይዞታ ስር የቆየና በላዩም ላይ አመልካች ቤት የሰራበት እንደሆነም ተረጋግጦአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቦታው ለአመልካች ከመሰጠቱ በፊት ማለትም ከ1982 ዓ.ም በፊትም ቢሆን በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር እንዳልነበረ፤ ይልቁንም የጦር ሰፈር አካል እንደነበረ በተጠሪው የክስ ማመልከቻ ጭምር መገለፁን ነው የተገነዘብነው፡፡



የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67 ከታወጀበት ቀን (1967) ጀምሮ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡ ግለሰቦች በከተማ ቦታ ላይ የመጠቀም ወይም የይዞታ መብት ሊኖራቸው የሚችለው በሚመለከተው የመንግሥት አካል በሕጋዊ መንገድ ሲሰጣቸው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም አከራካሪው ቦታ ከፍ ሲል በጠቀስነው አዋጅ ቁ.47/67 መሠረት የመንግሥት ንብረት የሆነው ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ነው በመሆኑም ሊያዝበት የሚችለው መንግሥት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ባዶ መሆኑ እና በማንም ሰው አለመያዙ ተረጋግጦ ለአመልካች ተሰጥቶአል፡፡ በ1945 ዓ.ም ለተጠሪ አባት ተሰጥቶ የነበረው ካርታም ከ1967ቱ አዋጅ ወዲህ ለተጠሪው አባትም ሆነ ለተጠሪው የሚሰጠው መብት የለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ቦታው በተጠሪው አባትም ሆነ በተጠሪው ይዞታ ስር የነበረ ለመሆኑ ወይም በእነሱ ይዞታ ስር እያለ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልቀረበ ተጠሪ ክስ ለመመስረት የሚችልበት ምክንያት እንኳን አልነበረውም፡፡ እኛ እንዳየነው ተጠሪ ክሱን የመሠረተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33(2) የግድ በሚለው መሠረት ክስ በመሠረተበት ቦታ ላይ መብት ያለው መሆኑን ከጅምሩ (ከመሠረቱ) ሳያረጋግጥ ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳው ፍ/ቤት ክሱን